# Learning by Ear 2013

"መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ–«መዘዙን መቀበል»

EPISODE 1: «ምን ባደርግ ይሻለል»?

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, ዳንኤል Pelz, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**SCENE 1: ትዕግስት AND ምህረት TALK AT BREAK**

- **ምህረት (F, 15)**
- **ትዕግስት (F, 15)**
- **GIRL (F, 15)**

**SCENE 2: ዳንኤል SKYPES WITH HIS FATHER**

- **ዳንኤል (M, 16)**
- **አቶ ካሳሁን (M, 50)**

**SCENE 3: ንጉሴ TALKS TO PEDDLER**

- **BOY (M, 15)**
- **PEDDLER (M, 35)**
- **ንጉሴ (M, 16)**
- **GUARD (M, 60)**

**SCENE 4: ብሩክ AND ቅዱስ PLAY IN TANDIKA**

- **ብሩክ (M, 8)**
- **ቅዱስ (M, 8)**

## INTRO

## 1. NARRATOR

**ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ተከታታዮች። "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ ለሚቀርብላችሁ ድራማ በሰዓቱ ደርሳችኋል። ዛሬ «መዘዙን መቀበል» የተሰኘውን የሁለተኛውን ዙር እንጀምራለን። ዘና ብላችሁ ተቀመጡና ምህረት፣ ዳንኤል እንዲሁም ንጉሴ የሚገጥማቸውን አድምጡ። ምናልባት ስለነሱ ያልሰማችሁ ካላችሁ እነዚህ ሶስት አፍሪቃውያን ወጣቶች የቦንጎ አካዴሚ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ናቸው። ባለፉት ሳምንታት በርካታ ነገሮችን መጋፈጥ ነበረባቸው። ምህረት ሙላቱ ከደሀ ቤተሰብ ነው የተወለደችው። ነገር ግን እድሜ ለነፃ የትምህርት ዕድል የቦንጎ አካዴሚን ተቀላቅላለች። የክፍሏ ልጅ ንጉሴ ጃለታም ወዲያው ነበር ከልቡ ያፈቀራት። ምህረት ግን ያን ያህል አልማረካትም:**

### *KW BEGIN*

## 2. SEASON 1, EPISODE 12, LINE 21 – 25:

*ምህረት: ንጉሴ አንድ ነገር ልነግርህ ነበር።*

*ንጉሴ: (…) በሁለመናዬ አዳምጥሻለሁ።*

*ምህረት: ንጉሴ, እኔ… እኔ… እኔ እንደሚመስለኝ የምወደው…*

*ንጉሴ: እኔም እወድሻለሁ ምህረት!*

*ምህረት: እኔ እንደሚመስለኝ የምወደው ዳንኤልን ነው።*

### *KW END*

## 3. NARRATOR:

*ምህረት ዳንኤልካሳሁንን መምረጧ ንጉሴን በጣም ነበር ያስከፋው። ይህ ብቻ አይደለም ለምህረት እና ቤተሰቦቿም ቢሆን ህይወት ቀላል ልትሆን አልቻለችም። አክስታቸው ወ/ሮ ለምለም ጋ ይኖሩ የነበሩት የምህረት ታናሽ መንታ ወንድሞች ቅዱስ እና ብሩክ ከጎረቤት ሀገር ላቦሪያ ገና መመለሳቸው ነው። ይሁንና የቤተሰቡ መዋሀድ ዘለቄታ አልነበረውም። የምህረት አባት አቶ ሙላቱ በዘረፋ ወንጀል ተጠርጥረው ፖሊስ አስረቸዋል። ይህም አልበቃ ብሎ ምህረትን ሌላ ችግር ገጥሟታል።*:

## 4. SEASON 1, EP. 26, LINES 38-44

*ምህረት: ዳንኤል አርግዤያለሁ። (…)*

*ዳንኤል: ኃላፊነት የለብኝም። በዛ ላይ አባት ለመሆን ዝግጁ አይደለሁም።(…)*

*ምህረት: እንዲህ ልትልማ አትችልም ዳንኤል።*

## 5. NARRATOR:

*ነገር ግን ዳንኤል የሚለውን የሚፈፅም ይመስላል። አባቱ ልጃቸው የቦንጎ አካዴሚን ለቆ ወደ ሀገሩ ላቦሪያ እንዲመለስ ይፈልጋሉ። ከኃላፊነቱ ለመሸሽ ጥሩ አጋጣሚ ነው አይደል? ስለ ዳንኤል እና ሌሎቹ ከሰማን ጥቂት ጊዜያት ተቆጥረዋል። እስቲ ሰሞኑን የሆኑትን መለስ ብለን እናስታውስ። « ምን ባደርግ ይሻላል?» ይላል የዛሬው ሁለተኛ ዙር የመጀመሪያ ክፍል ድራማ። ምህረት እና ጓደኛዋ ትዕግስትን በቦንጎ አካዴሚ የዕረፍት ሰዓት ላይ ሳሉ እናገኛቸው። ….*

**SCENE 1: ትዕግስት AND ምህረት TALK AT BREAK**

**6. ATMO: BONGO ACADEMY OUTSIDE AT BREAK**

**7. ምህረት:** **(regretfully)** ትዕግስት፤ እሺ አሁን ምን ላደርግ ነው? ወላጆቼንስ ምንድን ነው የምላቸው? ሰውስ ምን ይለኛል?

**8. ትዕግስት:** **(calmly)** ምህረት፤ እስቲ ተረጋጊ። ቀደም ብዬም ነግሬሻለሁ። ቀላል መፍትሄ አለው።

**9. ምህረት:** **(doesn’t seem to be listening)** ዳንኤል ማርገዜን ከነገርኩት ቀን አንስቶ አናግሮኝ አያውቅም።... ከዛ በፊት ግን አበድኩ ተቀበርኩልሽ ነበር የሚለኝ። ለምንድን ነው ይህን የሚያደርገው?

**10. ትዕግስት:** ምህረት፤ ባክሽ ሁሉም ወንዶች ናቸው ይህንን የሚሉት። ወንዶች ከኛ የሚፈልጉት አንድ ነገር ነው። ያንን እንዳገኙም ይተውናል። ልክ እንደ ቀድሞ ፍቅረኛዬ ምኞቴ፤ ትዝ ይልሻል ያ የታክሲ ረዳቱ?! የሚፈልገውን ካገኘ በኋላ ዞር በይ አለኝ። በዛ ላይ በግብረ ስጋ ግንኙነት ጊዜ የሚተላለፍ በሽታ አጋባብኝ። **(pause)** ባክሽ ተይው። ለማንኛውም አንቺ በቅርቡ መወሰን ያለብሽ ይመስለኛል። ... ገባሽ...?

**11. ምህረት:** ትዕግስት ነገሩ አልተመቸኝም ... ምን መሰለሽ። በዛ ላይ ለዶ/ር ዘሪሁን የምከፍለው ገንዘብ ከየት አገኛለሁ?

**12. SFX: STUDENTS PLAYING WITH A BALL NEARBY**

**13. ትዕግስት:** ዳንኤልን ጠይቂው። እርግጠኛ ነኝ ሊረዳሽ ፍቃደኛ ነው። በዛ ላይ ሰው ሁሉ ተጠያቂው እሱ እንደሆነ እንዲያውቅ አይፈልግም። ማለቴ ከዚህ ቀደም ገንዘብ ሰጥቶሽ ያውቃል አይደል?

**14. ምህረት:** **(Sighs)** አላውቅም ትዕግስት… እርግጠኛ አይደለሁም… እኔ….

***KW BEGIN***

**15. SFX: BALL HITS THEM**

**16. ምህረት:** ውይ!

**17. SFX: RUSTLING OF CLOTHES AS ትዕግስት GETS UP**

**18. ትዕግስት:** **(shouts)** ስሚ! ኳሳችሁን እዛው! እናውራበት እሺ።

**19. GIRL:** **(from far)** ይህ መጫወቻ ሜዳ እንጂ ሀሜት መዘብዘቢያ ቦታ አይደለም። ማውራት ከፈለጋችሁ ለምን ሽንት ቤት ሄዳችሁ አትለፈልፉም። እንጫወትበት አትበጥብጡን።

**20. ትዕግስት:** **(threatening)** ከአሁን በኋላ ኳስሽ ይንካንና ይህን ጨበሬ ፀጉርሽን ነው የምነጭልሽ።

**21. GIRL:** ነው፤ በያ ነይ እስኪ እንይሽ!

**22. ምህረት:** **(calming her down)** ትዕግስት ባክሽ ተያት እሷን…

***KW END***

**23.** ትዕግስት: **(to ምህረት)** ስሚ ምህረት። እናት ሆነሽ ወጣትነትሽ እንዲያመልጥሽ ትፈልጊያለሽ? እስቲ አስቢው ሁሉም ወንዶች በአንዴ የልጅ እናት እያሉ ሲጠሩሽ። ከዛ በኋላ ከእንቺ ጋ ጨርሶ የትም ቦታ አይሄዱም። በፍፁም--

**24.** ምህረት: **(cuts in)** እሺ ይበቃል! አቁሚ ቆይ ትንሽ ላስብበት እሺ?

**25. MUSICAL INTERLUDE**

**(OR FADE EXTERIOR BREAK ATMO TO INDOOR ATMO)**

**SCENE 2: ዳንኤል SKYPES WITH HIS FATHER**

**26. ATMO: ዳንኤል’S ROOM. BREAK ATMO HEARD FROM INSIDE**

**27. SFX: COMPUTER KEYS TAPPED, DIALLING TONE**

**28.** ዳንኤል: **(to himself)** ከአባዬ ጋ መነጋገር አለብኝ።... ኡፍ! ይህ የኢንተርኔት ስልክ ደግሞ... ሲመስለው ይሰራል ሲመስለው አይሰራም። ... ብቻ አንላይን በሆነ...

**29. SFX: SKYPE SOUND: CALLING**

**30. SFX: CALL ACCEPTED**

**31.** ዳንኤል: **(impatiently)** ታድያስ – አባዬ?

**32.** አቶ ካሳሁን: **(surprised, but severe)** ዳንኤል! ታድያስ የኔ ልጅ ትምህርት ላይ አይደለህም እንዴ?

**33.** ዳንኤል: አረፍት ላይ ነን። አባዬ እሱን ለኔ ተወው ብለህ ነበር ግን ለማንኛውም መመለሻ የበረራ ቲኬቴን ገዛህልኝ? --

**34.** አቶ ካሳሁን: **(interrupts him, strict and serious tone)** ዳንኤል አዝናለሁ የምነግርህ አስደሳች ዜና አይደለምም። ላቦሪያ ውስጥ ነገሮች ጥሩ አይመስሉም። **(sighs)** ጦርነቱ በመላው የአገሪቱ ክፍል እየተስፋፋ ነው።... ስለሆነም አሁን ብትመጣ ለደህንነትህ ጥሩ አይደለም።

**35.** ዳንኤል: ኧረ አባዬ፤ አይሆንም! አባዬ እባክህ...

**36.** አቶ ካሳሁን: አዝናለሁ ዳንኤል። ከእደኔ በላይ ያንተን መምጣት የፈለገ አልነበረም። ግን እዛው ያለህበት ብትቆይ ነው የሚሻለው።

**37.** ዳንኤል ግን አባዬ! እንደምትለው ይህን ያህል ከባድ አይመስለኝም። ሰዎች እንደሆነ መንግስትን በመቃወም ሁሌ የተቃውሞ ሰልፍ በላቦሪያ ሲያደረጉ ይሄ አዲስ አይደለም።

**38.** አቶ ካሳሁን: **(firm)** ያሁኑ ከበድ ያለ ነው። አማጺያኑ ኃይል አግኝተዋል። እኛ ደግሞ የመንግሥት አካል ነን። ያው የኛ የካሳሁን ቤተሰብ ሁሌም ከመንግስት ጋ በትብብር ሲሰራ ቆይቷል። መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ስለዚህ ነገሮች እስኪረጋጉ እዛው ኪሲምባ ብትቆይ ይሻላል።

***KW BEGIN***

**39.** ዳንኤል: ግን አባዬ ይሄ ትምህርት የመጨረሻ አስጠልቶኛል!

**40.** አቶ ካሳሁን: **(annoyed)** ምን አልክ? ወደ ቤትህ መመለስ እንደማትፈልግ ከነገርከኝ እኮ ምንም ያህል ጊዜ አልሆነም።

**41.** ዳንኤል: እኔ… እኔ… --

**42.** አቶ ካሳሁን: ዳንኤል አንተን ወደዚህ አምጥቼ አማኢያን እንዲይዙህ ወይንም እንዲያስሩህ ኋላፊነት መውሰድ አልችልም። አሁን ራሱ ከፊል ማዕድናችንን እና ሰራተኞቻችንን አጥተናል። በአሁኑ ሰዓት በጣም አደገኛ ነው። ያለውን ነገር ከርዕሰ መምህርትህ ጋ ተነጋግሬ ሀሳቡን ተቀብላለች።

***KW END***

**43.** ዳንኤል: ግን አባዬ…

**44.** አቶ ካሳሁን: **(decidedly)** ምንም ግን የለም። አለቀ። እኔ ሀሳቤን እስክቀይር ድረስ በቦንጎ አካዴሚ ትቆያለህ።

**45.** ዳንኤል: **(scared)** ግን አባዬ… አንተ እና እማዬስ?

**46.** አቶ ካሳሁን: ስለእኛ አታስብ። እኛ ምንም አንሆንም። በል ደህና ሁን። ቻው።

**47. SFX: LINE DISCONNECTS**

**48.** ዳንኤል: አባዬ ቆየኝ ቆየኝ ..ኡፍ ምን አይነት ነገር ነው!

**49. MUSICAL INTERLUDE**

**(OR FADE BREAK ATMO FROM INSIDE TO OUTSIDE)**

**SCENE 3: ንጉሴ TALKS TO PEDDLER**

**50. ATMO: BONGO ACADEMY AT BREAK, OUTSIDE**

**51. ንጉሴ:** **(to himself)** እንደው ይህ የትምህርት ቀን አልፎ ብቻ። የቦንጎ አካዴሚ እንዴት ይደብራል። …

***KW BEGIN***

**52. SFX: STEPS APPROACHING (ON GRASS)**

**53. BOY:** ታድያስ ንጉሴ እንዴት ነው?

**54. ንጉሴ:** **(flatly)** ደህና ነኝ።

**55. BOY:** ለምንድን ነው እዛ ጋ ብቻህን ዱቅ ያልከው። ፈታ በል እባክህ። **(jokes)** እርግጠኛ ነኝ በጠበጠ ብሎ ማንም አያስርህም። **(laughs)** ና እና ከኛ ጋ ተቀላቀል።

**56. ንጉሴ:** እሺ ምናልባት በኋላ…

**57. SFX:STEPS LEAVE**

**58. BOY:** **(leaves)** ሀ ሀ ምናልባት ስለምትደበር – ትታሰር ይሆናል።…

***KW END***

**59. PEDDLER:** **(from a distance)** እስ! እስ! ንጉሴ! ንጉሴ!

**60. ንጉሴ:** **(to the man, in a hushed voice)** እሺ ጠብቀኝ መጣሁ!

**61. SFX: RUSTLING OF CLOTHES (ንጉሴ GETS UP)**

**62. SFX: RUNNING FOOTSTEPS ON GRASS**

**63. SFX: BREAK ATMO LOWER, TRAFFIC ADDED**

**64. ንጉሴ:** **(keeps his voice down)** የትምህርት ቤቱ አጥር ስር ምን ትሰራለህ? ትምህርት ቤት ድረስ እንዳትመጣ አልነገርኩህም?!

**65. PEDDLER:** ገንዘቤን ፈልጌ ነው የመጣሁት።

**66. ንጉሴ:** ርዕሰ መምህሯ ብታየኝ ምን የምታደርግ መሰለህ? ለዛውም ከ... ከ...

**67. PEDDLER:** **(threatening)** ምን? ከእፅ ነጋዴ ጋ? የኔን ጋንጃ ሳትከፍል ከማጨስህ በፊት ስለዚህ ልታስብበት ትችል ነበር።

***KW BEGIN***

**68. ንጉሴ:** **(begging)** በእናትህ አሁን ያለኝ 50 ሳንቲም ብቻ ነው። በኔ ይሁንብህ ገንዘብ እንዳገኘሁ እከፍልሃለሁ።

**69. PEDDLER:** **(threatening)** ገንዘቤን እስካገኝ ድረስ ከዚህ ቦታ አልንቀሳቀስም ንጉሴ! አጭሰሀል! ትከፍላለህ!

**70. ንጉሴ:** ባክህ ነፍሱ። ቤተሰቤን ታውቃቸዋለህ። ገንዘብ አለን። እና 10 ዶላር ማግኘት ለኔ ይሄን ያህል ከባድ ሆኖ አይደለም።...

**71. PEDDLER:** እና እንደሱ ከሆነማ ለምን እስካሁን አልከፈልክም?

***KW END***

**72. ንጉሴ:** **(panics)** ዘበኛው ወደዚህ እያየ ነው። በእናትህ ሂድ። ነገ እከፍልሀለሁ። በእውነት።

**73. PEDDLER:** ይሻልሀል!

**74. SFX: STEPS PEDDLER LEAVING**

**75. GUARD:** **(shouts from afar)** ስማ! አንተን እኮ ነው? አጥሩ ስር ምን ታደርጋለህ? ዞር በል ከዚህ።

**76. ንጉሴ:** **(appeasing)** እሺ እሺ ዘብ **(to himself)** ወይኔ ለትንሽ፤ አክትሞልኝ ነበር!

**77. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 4: ብሩክ AND ቅዱስ PLAY IN TANDIKA</u>**

**78. ATMO: TANDIKA SLUMS OUTSIDE, DAYTIME**

**79. SFX: PLASTIC BALL KICKED AS THEY PLAY FOOTBALL**

**80. ብሩክ:** **(coughs)** ቅዱስ ወንድሜ፤ ወደቤት ተመልሶ እንደገና ውጪ መጫወት መቻል አሪፍ ነው አይደል?

**81. ቅዱስ:** ቀላል ብሩክ። ምናልባት እህታችን ምህረት ከትምህርት ቤት ስትመለስ አብራን ልትጫወት ትችላለች።

**82. ብሩክ:** **(laughs)** ምህረት ኳስ መጫወት አትችልም።

**83.** ቅዱስ: **(laughs too)** ምናልባት እኛ እዚህ ባልነበርንበት ወቅት ተምራ ይሆናል።**(suddenly sad)** አባዬ ቢኖር እንዴት ጥሩ ነበር።

**84.** ብሩክ: እኔስ ብትል። እማዬ ግን በቅርቡ ይመለሳል ብላኛለች።

**85.** ቅዱስ: ግን ለምንድን ነው ከፓሌ እና ከዛ ትልቅ ቆንጆዬ ቤት የለቀቅነው?

**86.** ብሩክ: እማዬ፤ አባዬ ስለሌለ ክፍያውን አልቻልኩትም ብላ ነው ።

**87.** ቅዱስ: እእእ። እሺ ኳሷን አቀብለኝ። እንዴት ግብ እንደማገባ አሳይሀለሁ።

**88. SFX: FOOTSTEPS RUNNING (ቅዱስ)**

**89.** ብሩክ: **(coughs and shouts)** እሺ። ቅዱስ ተመልከት ጎሉን አስፍቼልሀለሁ።

**90. SFX: ቅዱስ KICKS PLASTIC BALL**

**91.** ብሩክ: **(laughs)** በእስምዓም። እንደ ሴት ነው የምትለጋው። በረኛ ባይኖር እንኳን ጎል አታስቆጥርም። ምህረት ከአንተ የበለጠ ሳትጫወት አትቀርም።

**92.** ቅዱስ: **(sulks)** ክፉ ነህ ብሩክ። ልክ ላቦሪያ ማዕድን ማውጫ እንዳሉት ልጆች።

**93. SFX: THUNDER IN THE DISTANCE**

**94.** ብሩክ: **(suddenly serious)** ቅዱስ፤ ስለ ማዕድን ማውጫው ለማንም መንገር የለብንም። ይህንን ነው አክስት ለምለም እና አቶ ካሳሁን የነገሩን።

**95.** ቅዱስ: እና እነሱ እዚህ የሉ። ሊሰሙን አይችሉም።

**96.** ብሩክ: ምናልባት ሰላይ ይኖራቸው ይሆናልዋል። ገባህ ልክ ፊልም ላይ እንደምናየው። … **(coughs)**

**97. SFX: LOUD THUNDER, IT STARTS TO RAIN**

**98.** ብሩክ: ና! መዝነብ ጀምሯል። ከመበስበሳችን በፊት ወደ ቤት እንሩጥ።

**99.** ቅዱስ/ብሩክ **(THEY LAUGH)**

**100. SFX: FOOTSTEPS (2 PERSONS) RUNNING ON WET GROUND**

**101. OUTRO - NARRATOR**

እኛም ለዛሬ ያልነው የእካሁኑ ነበር። የምህረት ወንድሞች ቅዱስ እና ብሩክ እየተሳቁ ወደቤታቸው በመሮጥ ላይ ናቸው። ምንም ይሁን ምን ግን በላቦሪያ ይገጠማቸውየነበረው የሚያስቅ አልነበረም። ታዲያ እነሱ ብቻ አይደሉም በውስጣቸው ምስጥር የያዙት። …ስለ ዳንኤል፣ ምህረት እና ሌሎቹ ማወቅ ትፈልጋላችሁ? እንግዲያውስ dw.de/lbe የሚለውን ድረ ገፃችንን ጎብኙ። እዛ ውስጥ አዲስ የቪዲዮ ዘገባም ታገኛላችሁ። በአሁኑ ዳንኤል አይደለም ስለራሱ የሚዘግበው - እ… **(smiling)** አይ… አሁን ከነገርኳችሁማ ሚስጥር መሆኑ ይቀራል። እናንተው ድረሱበት። የሚቀጥለውን ቀጣይ ድራማ መስማት እንዳትረሱ። በፌስ ቡክም ልትከታተሉ እና አስተያየታችሁን ልታካፍሉን ትችላላችሁ። እስከሚቀጥለው ጊዜ! ደህና ሁኑ!